# ኢትዮጵያ

የሰብአዊ መብቶች አያያዝ፥ የየሀገሩ ዘገባዎች /ሪፖርቶች/ ማርች 6 ቀን 2007 ዓ.ም. በዴሞክራሲ፥ በሰብአዊ መብቶች እና ሠራተኛ ጉዳይ ጽ/ቤት ይፋ ተደረገ።

ኢትዮጵያ በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊና በገዥው በኢህአዴግ ጥምር ፓርቲዎች የምትመራ ፌደራላዊ ሬፑብሊክ የሀገሪቷ ሕዝብ ቁጥር በግምት 77 ሚሊየን ነው። በ2005ቱ ጁን የምክር ቤት ምርጫ ኢሕአዴግ በተከታታይ ለሦስተኛ ጊዜ ሀገሪቷን ለአምስት አመት ለማስተዳደር አሸንፏል። የሃገር ውስጥና አለም አቀፍ ታዛቢዎች ምርጫው እዚያና እዚህ አንዳንድ ጉድለቶች ቢታዩበትም ባጠቃላይ በትክክለኛና ባስተማማኝ ሁኔታ የተካሄደ እንደነበር የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል።

ፖለቲካ ፖርቲዎች በአመዛኙ በብሔር ብሔረሰብ የተደራጁ ነበሩ። ነገር ግን ተቀዋሚዎች ቀስ በቀስ የጥምር ፓርቲ የመመሥረት ሂደት አሣይተዋል። የመንግስት ባለሥልጣናት በፀጥታ ኃይሎች ላይ የተዋጣለት ቁጥጥር እያደረጉ ሣለ በፀጥታ ኃይሎች የታቀፉ አንዳንድ ግለሰቦች መንግስት ከፈቀደላቸው መመሪያ ውጪ ተንቀሳቅሰዋል። ባመቱ ውስጥ የተዘገቡ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች የሚከተሉትን ድርጊቶች ያካተቱ ነበሩ። በቅርብ በተካሄዱ ምርጫዎች መንግስታቸውን ለመለወጥ የፈለጉ ዜጐችን መብት መገደብ፣ የሕግ ድጋፍ ሣይኖር ሰዎችን መደብደብና መግደል፣ ያለምክንያት የሰውን ክብር ለመንካትና በማቆያ ቤት ያሉ ግለሰቦችንና የተቃዋሚ ደጋፊዎችን በፀጥታ ሀይሎች ያላግባብ እንዲጉላሉ ማስደረግ።

ብዙ ነገር በጉደላቸው እሥር ቤቶች ውስጥ በሥር ማቆየትና ሰዎችን ሳይከሰሱ ይዞ የማሠር ተግባራት ተከስተዋል። እነዚህ ተግባራት በተለይ የተቃዋሚዎች አባላት ወይም ደጋፊዎች ሳይሆኑ አይቀርም ተብለው በተጠረጠሩ ሰዎች ላይ ተፈጽመዋል። በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሰዎች ፍርድ ቤት ከመቅረባቸው በፊት ለብዙ ጊዜ በስር ላይ ቆይተዋል። የዜጎች በግል የመኖር መብትና ሕጉ ያስቀመጣቸውን የፍተሻ መመሪያዎች ደጋግሞ አለመከተል፣ በፕሬስ ነፃነት ላይ ገደብ ማበጀት፣ ያለምክንያት ሰዎችን መያዝና በሥር ማቆየት፣ መንግስትን የሚተቹ ጽሁፎችን የሚያወጡ ጋዜጠኞችን ማስጨነቅ፣ በመሰብሰብ ነፃነት ላይ ማነቆ ማበጀት፣ በማህበር የመደራጀት ነፃነት ላይ ገደብ መጣል፣ ሴቶችን ከማሕበራዊ ሕይወት ማግለልና የሕፃናትን መብት አለማስከበር፣ የሴቶች ግርዛትን አለማስቆም፣ ለኤኮኖሚ ጥቅም ማግኛነትና ለወሲብ ጥቃት ሲጋለጡ በቸልታ ማየት፣ ሰዎችን ማዘዋወር፣ አካል ጉዳተኞችን፣ የሃይማኖትና የአናሣ ብሔረሰቦች በጉዳተኝነታቸውና ውሁዳን በመሆናቸው ብቻ በማህረሰቡ መድሎ ሲፈፀምባቸው ዝም ብሎ ማየትና በማህበራት እንቅስቃሴዎች ውስጥ የመንግስት ጣልቃ መግባት የተለመዱ ተግባራት ነበሩ።

ክፍል አንድ፣

ሰብአዊ መብቶችን ማክበር የሰውን ምልኡጋት ማክበር፥ ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፥

ሀ - በዘፈቀደ ወይም ከሕግ ውጭ ሕይወትን ማሳጣት፥ ባለፈው አመት እንደተፈፀሙት ያሉ ግድያዎች በዚህ ዓመት የፖለቲካ መንስኤ የነበራቸው ግድያዎች አልነበሩም። ይሁን እንጂ የፌደራልና ያካባቢ ፖሊስ ኃይሎች ባመቱ ውስጥ ከሕግ ውጭ ግድያዎችን ፈፅመው ነበር ።

ጃንዋሪ 23 በምስራቅ ወለጋ ዞን ጉድሩ ወረዳ ወስጥ የፌደራል ፖሊስ 15 ሕዝበ ትዕይንት አድራጊዎችን ተኩሶ ሲገድል። 19 በሚሆኑት ላይ ደግሞ ጉዳት አደረሰ። ተኩስ የተከፈተው ባካባቢ የመንግስት ኃይሎችን ለመቃወም ሰልፍ በወጡ ነዋሪዎች ላይ ነው። በደረሰው አጋጣሚ ላይ የተካሄደ ምንም ዓይነት ምርመራ የለም።

ማርች 6 ከስራ ውጪ የነበረና ዓለሙ ድሪባ የተባለ ፖሊስ መኮንን ካልታወቁ ግብረአበሮቹ ጋር ሆኖ በጎንደር ከተማ 4 ወጣቶችን ገድሏል። ዓለሙ የ17 ዓመቱን በረከት ፋንታሁንን፣ የ18 ዓመቱን አበበ ወንድማገኝን፣ አሁንም የ18 ዓመቱን ስንታየሁ ወርቅነህንና የ19 ዓመቱን ዳዊት ተስፋዬን ቀርቦ እጃቸውን ወደ ላይ እንዲያነሱ አዘዛቸው ይባላል። ከዚያም በ30 ያርድ ርቀት ላይ ወደሚገኝ ወንዝ ወስዷቸው፣ መሬት ላይ እንዲተኙ ካደረጋቸው በኋላ የእያንዳንዳቸውን እራስ በጥይት እየመታ ገደላቸው። ዓለሙም ከጥቂት ሰዓታት በኋላ በቁጥጥር ሥር እንዲውል ተደርጐ ክስ ሣይመሠረትበት ዓመቱን ጨርሷል።

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ እንደዘገበው በግንቦት 27 ***በኦሮሚያ*** ክልል

***ናዝሬት*** ከተማ በሱቅ ባለቤቶችና በፖሊሶች መካከል በተቀሰቀሰ ግጭት የተነሣ ፖሊስ◉ ዓለሙ ተስፋዬ፣ ታሪኩ ያኪሰና መንሱር ሙሰማ የተባሉ ሰዎችን በጥይት ተኩሶ ገድሏቸዋል። ፖሊስ ከይዞታቸው ሊያስነሣቸው ሲሞክር ባለቤቶቹና ሠራተኞቻቸው በፖሊሶቹ ላይ ድንጋይ በመወርወር የአፀፋ ርምጃ ወስደዋል። የተከሰተውን ግጭት አስመልክቶ ምንም ዓይነት የማጣራት ሥራ አልተሰራም።

በ2005 ኦገስት ላይ ***በጊቤ*** ወረዳ ኤልያስ ሞላንጐ በጦር ሰራዊት አባላት እንደተገደለ ሪፖርቶች ደርሰዋል።

ኤልያስ ከተገደለ በኋላ አስከሬኑ ***ለሆሣዕና*** ከተማ ነዋሪዎች በግልጽ እንዲታይ ተደርጓል። ኤልያስ በ2000ው የተወካዮች ምክር ቤት አባላት ምርጫ ላይ በታዛቢነት ሠርቷል። በኋላም ለገዥው ፓርቲ አሸናፊነት አጕናጽፎታል የተባለውን የምርጫ ውጤት ተቃውሞ ነበር። ስለ ግለሰቡ ግድያ የተደረገ ሕጋዊ የማጥራት ሥራ ምንም የለም።

በ2005 ስለ መላው ኢትዮጵያ አንድነት ፓርቲ ቅንጅት አባላት የፖለቲካ ግድያዎች በተለይ ስለ አንለይ አዲስ፣ አየልኝ ወንድምነህ፣ ጥላሁን ከበረና አላምር አእምሮ ግድያዎች ምንም የሚታወቅ ነገር የለም። በ2005 መጨረሻ ፖሊስ ጥላሁን ከበረን ገድለዋል የተባሉ ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ስር አውሏል። ይሁን እንጅ ከዚያ በኋላ ጉዳዩ በምን ደረጃ ላይ ተይዞ እንዳለ የሚያስረዳ መረጃ የለም። በ2005 በፖሊስ፣ በሚሊሺያና በቀበሌ ባለሥልጣናት ስለተፈፀሙ የፖለቲካ ግድያዎች እስከ ዛሬ የተሰጠ ምንም መረጃ የለም። በጊዜው 24 የኦሮሞ ኮንግሬስ ፓርቲ አባላት ተገድለዋል። ከነዚህ ውስጥ አህመድ አደም የተባሉ ግለሰብና የምክር ቤት ተመራጭ የነበሩት የተከበሩ አቶ ተስፋዬ አዳነ ይገኙበታል። ባመቱ መጨረሻ በአቶ ተስፋዬ አዳነ ግድያ እጃቸው አለበት የተባሉ ተጠርጣሪዎች በዝዋይ ታስረው ነበር። ነገር ግን ጉዳያቸው በምርመራ ደረጃ እንደነበረ ቀረ። በ2005 በአማራ ክልል የቅንጅት ፓርቲ የምርጫ አስተባባሪ የነበረው የሀሰን እንድሪስ ግድያ ወይም ደግሞ በኦሮሚያ ክልል በግንቦት ወር የተገደሉት የሸክ ኡስማን ሐጂ አብደላ ጉዳይ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አይታወቅም። ሁለቱም ግድያዎች የተፈፀሙት በቀበሌ ባለሥልጣናት ነው።

ኦገስት ወር 2005 በበዘላ ሎምቢሶ ላይ በወታደሮች ስለተፈፀመው ግድያና ስለ ሚስቱ መደፈር እስከ ዛሬ የሚታወቅ ነገር የለም። በዘላ በ2000ው የብሔራዊና የክልል ምርጫዎች ጊዜ አንድ የፖሊስ አባል ገድሏል ተብሎ ተከሶ ነበር።

ሴብቴምበር 2005 የቅንጅት አባል በነበሩት በአቶ አሰፋ ጌታሁን ላይ የተፈፀመውን ግድያ፤ ኦክቶበር 2005 በግርማ ብሩ ላይ የተደረገውን የፖለቲካ ግድያ ወይም የሞሴ ዋሴና የጥላ ፀጋን ሕገወጥ ግድያ በተመለከተ ምንም ዓይነት መረጃ አልነበረም ።

በ2004 በፀጥታ ኃይሎች ተገድለዋል ስለተባሉት ከዚህ በታች ስማቸው ስለተዘረዘሩት ሰዎች ግድያም ቢሆን የታየ ይህ ነው የሚባል ርምጃ አልተወሰደም። በሶማሌ ክልል የተፈፀመው የከበደ ኡዞ ግድያ፤ በኦሮሚያ ክልል የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ በነበረው በአለሙ ተስፋዬ ግድያ ፤እዚያው ኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሁለተኛ ደረጃ